

# የኖህ ሚስት

- በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ክፋት እጅግ እየበዛ ስለሄደ እግዚአብሔር አዘነ። አንድ ሰው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን አገኘ። ማለትም እግዚአብሔር በዚህ ሰው እጅግ በጣም ደስተኛ ሆነ። የዚህ ሰው ስም ኖህ ይባል ነበር። ኖህ ፃድቅ ሰው ሲሆን እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘ የሚኖር ሰው ነበር። እግዚአብሔርም ኖህን በሰዎች ክፋት ምክንያት ምድርን እንደሚያጠፋትና ኖህንና ቤተሰቡን ግን ከዚህ ጥፋት እንደሚያድናቸው ቃል ገባለት።

- ቤተሰቡንና እንስሳትንም ለማዳንም  መርከብ እንዲያዘጋጅ አዘዘው። እግዚአብሔርም፣ “ከአንተ ጋር ቃልኪዳኔን አደርጋለሁ። አንተ፣ ልጆችህ፣ ሚስትህና የልጆችህ ሚስቶች ወደመርከቡ ትገባላችሁ።” ኖህ እንዴት መርከቧን እንደሚሰራም ግልፅ መመሪያ ሰጠው።

- የኖህን ሚስት ስም አናውቅም። ምክንያቱም ስሟ በመፅሐፍ ቅዱስ አልተገለፀምና። አንዳንድ ሰዎች ዘፍጥረት 4፡22ን መሠረት አድርገው ስሟ “ናዕማ” ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። እርግጠኞች መሆን ሰለማይቻልም ከዚህ በኋላ “የኖህ ሚስት” እያልን እንጠራታለን።

- መቼም ልክ በእግዚአብሔር ጠንካራ እምነት እንደነበረው እንደባሏ የኖህ ሚስትም  የእምነት ሴት እንደሆነች እርግጠኞች ነን። ሶስቱ ልጆቻቸው ማለትም ሴም፣ ሀምና ያፌት የተወለዱት ኖህ የ500 ዓመት ሰው ሲሆነው ነበር። የኖህ ሚስትም በዚያን ጊዜ እንዳረጀች ይታሰባል። ልጆቿንም እግዚአብሔርን እየፈሩ እንዲኖሩ አድርጋ እንዳሳደገቻቸው እርግጠኞች ነን። እነኝህ የኖህ ልጆች አባታቸውን በመርከብ ስራ ወቅት ይረዱት ነበር። የመረጧቸው ሚስቶቻቸውም በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው እምነትና አባታቸውን በመርከቡ ስራ ሲያግዙት የሚያበረታቷቸው እንጂ እንቅፋት የሚሆኑባቸው እንዳይሆኑ በጥንቃቄ መርጠዋቸዋል።

- የኖህ ሚስት በጣም ታጋሽ ነበረች ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ኖህ መርከቡን ሰርቶ ለመጨረስ በጣም ረጅም አመታትን ወስዶበታል። ምናልባትም 100 ዓመት ወይንም ከዚያ በላይ። ይህንንም የምናውቀው መርከቡ ተሰርቶ ሲያልቅ ኖህ የ600 ዓመት ሰው ነበር።

- የኖህ አባት ላሜሕና አያቱ ማቱሳላህ ሁለቱም የመርከቡ ስራ በተጀመረበት ወቅት በሕይወት ነበሩ። ነገር ግን የጥፋት ውሃ ከመምጣቱ በፊት ሞተዋል። ላሜህ የጥፋት ውሃ ከመምጣቱ ከ5 አመት በፊት ሲሞት ማቱሳለህ ግን የጥፋት ውሃ ሊመጣ አካባቢ በሕይወት ነበር። ሆኖም የጥፋት ውሃን አላየም። ስለዚህ ኖህ መርከቡን በሚሰራበት ጊዜ በሕይወት ከነበሩት ዘመዶቹ ትልቅ ድጋፍ ያገኝ ነበር። የኖህን ታናናሽ ወንድሞችና እህቶች በተመለከተ የሚታወቅ ነገር የለም።

- መቼም ኖህ መርከቡን ሲሰራ የሚያላግጡበትና ሞኝ አድርገው የሚቆጥሩት ሰዎች እንደነበሩ ይታሰባል። የኖህ ሚስትም ይህን የሰዎችን ማላገጥና ፌዝ ታግሳ እንዳሳለፈችው እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

- የጥፋት ውሃ ሲመጣም ቤተሰቡ በሙሉ ወደመርከቧ ገቡ። ዝናቡ የዘነበው ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት ነበር። ዝናቡ ቆሞ ውሃው እስከሚጎድልና ደረቅ መሬት እስከሚታይ ድረስ ረዥም ጊዜ ወስዶአል። መርከቡ ለኖህና ለቤተሰቡ ለአንድ ዓመትና ለ10 ቀናት እንደመጠለያ አገልግሏቸዋል። እስኪ ራሳችሁን ከተለያዩ እንስሳት ጋር አብራችሁ ለረዥም ጊዜ በመርከብ ውስጥ ሆናችሁ አስቡት።

- ውሃው ጎድሎ ደረቅ መሬት ከተገለጠ በኋላ ኖህና ቤተሰቡ መርከቡን ለቀው ወጡ። ከመርከብ ከወጡ በኋላ ኖህ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር ቢኖር መሰዊያን አበጅቶ ንፁህ እንስሳትን ለእግዚአብሔር መሰዋት ነበር። አንዳንዶች፣ “ኖህ እኮ ወደ መርከቡ ይዞ የገባው ከእያንዳንዱ የእንስሳት ዝርያ ሁለት ሁለት ብቻ ስለሆነ ይህ ከእውነት የራቀ ነው፣” ይሉ ይሆናል። ይህ አባባል ግን ትክክል አይደለም። በመፅሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው ከሆነ እግዚአብሔር ኖህን ለመስዋዕት ከሚሆኑ ንፁሕ እንስሳት ዝርያዎች ሰባት ሰባት፣ ንፁሕ ካልሆኑና ለመስዋዕት ከማይፈለጉ እንስሳት ዝርያዎች ደግሞ ሁለት ሁለት ብቻ ይዞ እንዲገባ አዞታል።

- ከመርከብ ከወጡና መስዋዕት ካቀረቡ በኋላ ወደሰማይ ቀና ብለው ሲመለከቱ በጣም የሚያምር ቀስተ ደመና አዩ። ያም እግዚአብሔር እንደገና ምድርን በጥፋት ውሃ እንደማያጠፋት የእግዚአብሔር ቃልኪዳን ምልክት ነበር።

*የኖህ ሚስት ታሪክ የሚገኘው በዘፍጥረት ከምዕራፍ 6 እስከ ምዕራፍ 9 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*